# የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት የፕሮግራም ምዝገባና የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

521/2013

ትምህርት ሚኒስቴር

ሰኔ 2003

አዲስ አበባ

መግቢያ........................................................................................ 1

አውጪው ባለስልጣን................................................................................ 2

አስፈፃሚ አካል...................................................................................... 2

## ክፍል አንድ

1. አጠቃላይ........................................................................................ 3

11 አጭር ርዕስ...................................................................................... 3

1.2 የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን........................................................................ 3

1.3 ትርጓሜ.......................................................................................... 3

## ክፍል ሁለት

2. የምዝገባና የእውቅና ፈቃድ መሰረታዊ ነጥቦችና ጽንሰ ሀሳብ........................................ 5

2.1 ምዝገባን አስመልክቶ የቀረቡ መሰረታዊ ነጥቦችና ጽንሰ ሀሳብ........................................ 5

2.1.1 የገበያ ፍላጎት መረጃ.............................................................................. 6

2.1.2 የሰው ሀብት...................................................................................... 6

2.1.3 የስልጠና አቅርቦቶች.............................................................................. 7

2.2 የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መሰረታዊ ነጥቦችና ጽንሰ ሀሳብ........................................ 7

## ክፍል ሦስት

3. የምዝገባ ፈቃድ.................................................................................... 9

3.1. ለምዝገባ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ሊይዛቸው የሚገቡ መስፈርቶች................................ 9

3.1.1የተቋሙ ራዕይ ተልዕኮ አላማና አሰራር.............................................................. 9

3.1.2 አስተዳደራዊ ሰነዶች.............................................................................. 9

3.1.3 የስርአተ ትምህርት መስፈርቶች.................................................................... 10

3.1.4 የስልጠናና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች................................................................ 11

3.1.5 የማሰልጠኛ ተቋማት አቅርቦቶች ........ 1

3.1.6 የማሰልጠኛ ተቋማት ሕንፃዎች ........ 1

3.1.7 የመማሪያ ክፍሎች ........ 15

3.1.8 ወርክሾፖች ሰርቶ ማሳያዎች ........ 15

3.1.9 ቤተ-መፃሕፍት ........ 16

3.1.10 የስፖርትና የመዝናኛ ማዕከሎች ........ 16

3.2 መመሪያዎች ........ 16

3.3 ደጋፊ መመሪያዎች ........ 17

3.4 የምዝገባ ማመልከቻ መገምገሚያ መስፈርቶች ........ 17

3.5 የምዝገባ ክፍያ ........ 18

3.6 የምዝገባ ፈቃድ ስለመስጠት ........ 19


## ክፍል አራት


4. የዕውቅና ፈቃድ ........ 20

4.1 የዕውቅና ፈቃድ መገምገሚያ መስፈርቶች ........ 20

4.2 ለዕውቅና ፈቃድ መሟላት ያለባቸው ነጥቦች ........ 21

4.3 የዕውቅና ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ........ 22

4.4 የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት ........ 22

4.5 የዕውቅና ፈቃድ ስለመሰረዝ ........ 23


## ክፍል አምስት


5. የዕውቅና ዕድሳት ........ 24

5.1 የዕውቅና ዕድሳት መገምገሚያ መስፈርት ........ 24

5.2 የዕውቅና ዕድሳት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚይዛቸው ነጥቦች ........ 25

5.3 የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ስለመስጠት ........ 25

5.4 የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ክፍያ........................................................................ 26

## ክፍል ስድስት

6. የማታና የርቀት ትምህርትና ስልጠና........................................................................ 27

6.1 የርቀት ትምህርትና ስልጠናን በተመለከተ........................................................................ 27

6.2 የማታ ስልጠናን በተመለከተ........................................................................ 27

## መግቢያ

በ1987 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለውን የአገራችንን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ የግልና የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በአገራችን ተስፋፍተው ብዛት ያላቸው ሰልጣኞች በተለያዩ የሙያ መስኮች ሰልጥነው የወጡ ቢሆንም የስራው አለም ከዘርፉ የሚጠብቀውን እስከ መካከለኛ ደረጃ ድረስ የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው የብቃት ደረጃና የሙያ መስክ እንዲሁም የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ አልተቻለም፡፡ በተለይም ደግሞ የዚህ ዘርፍ አጠቃላይ ግብ የሆነውን ማለትም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተመራቂዎች ስራ ፈጣሪዎች ሆነው እራሳቸውንና አገራቸውን ማሳደግ የሚችሉ ዜጎችን የመፍጠር ግብም ማሳካት አልተቻለም፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቱ የስልጠና ስርአቱ ከውጤት ይልቅ ግብአት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ነው የሚል እምነት አለ፡፡ ይህም በስልጠናው ጥራት ላይ ቀላል የማይባል ችግር ከማስከተሉም ባሻገር ብቃት በሌላቸው የሙያ ተመራቂዎች አማካኝነት የሚከናወኑት ተግባራት የተገልጋዩን ህብረተሰብና የኢንዱስትሪው ፍላጎት ማርካት አላስቻለም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የስልጠና ጥራት መቆጣጠሪያ መሣሪያ ከሆኑት አንዱ የሆነው የቅድመ እውቅናና የእውቅና ፈቃድ አሰጣጥ ስርአትም በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንዱስትሪው ተፈላጊ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም የስልጠናው ውጤትንና ፋይዳን በዋናነት መሠረት ከማድረግ ይልቅ የስልጠና ግብአት /የማሰልጠኛ ቁሳቁስ፣ የመምህራን ፕሮፋይል፣ ወዘተ/ ላይ ብቻ ያተኮረ ሆኖ በመቆየቱ ነበር፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በመቅረፍ ኢንዱስትሪው በሚፈልገው የሙያ ዘርፍና መጠን አገራችን የምትፈልገውን ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና የወጠነችውን የሃገር የእድገት ስትራቴጂና ፖሊሲ ተረድተው ለማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ባለሙያዎችን ለመፍጠር እና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ኢንዱስትሪው በአለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ተወዳዳሪነት ለማጎልበት በሚያስችል ሁኔታ የሌሎች አገሮች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመፈተሽና ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ቃኝቶ በመቀመር አገር አቀፍ የቴ/ሙ/ት/ስ ስትራቴጅ ተቀርፆ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል፡፡

ለዚህ ስትራቴጂ ስኬት ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና የእውቅና አሰጣጥ ስርአቱ በቴ/ሙ/ት/ስ ዘርፍ የተሰማሩ ተቋማትን በማብቃት ላይ ያተኮር ድጋፍ የሚሰጥና የሚያበረታታ የእውቅና አሰጣጥ መዋቅር በመዘርጋት ለቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የጥራት ደረጃ መመዘኛ መስፈርት ማስቀመጥ፣ ተቋማቱ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ አሟልተው እንዲገኙ ችግሮቻቸውን ለይቶ በማወቅ ድጋፍ መስጠት እና የስኬታቸውን ደረጃ መገምገም፡ሰልጣኞች የጥራት ደረጃውን ካልጠበቀ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና አቅርቦት እንዲጠበቁ በማድረግ በዘርፉ ገበያ ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርአት እውን ማድረግ እንዲቻል ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል::

## አውጪው ባለስልጣን

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ የቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 198/2003 አንቀጽ 6 ንዑስ ንቀፅ 7 መሰረት እና በ1999 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ስራ ላይ የዋለውን አገር አቀፍ የቴ/ሙ/ት/ስ ስትራተጅን መሠረት በማድረግ የፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት የሚሰጡትን ስልጠና የፕሮግራም እውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አስፈፃሚ አካል

በቴ/ሙ/ት/ስ አዋጅ ቁጥር 391/96 አንቀጽ 32 ንዑስ 1 መሠረት በፌደራል መንግስት አካላት ስር ወይም በውጭ አገር ባለሀብት ወይም በውጭ ሀገር ህግ መሰረት በተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ለሚካሄድ የማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ (የፕሮግራም ምዝገባ እና የእውቅና ፈቃድ) የመስጠት ስልጣን የኤጀንሲው ይሆናል፡፡

- በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በክልል የመንግስት አካላት ስር ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ሀገር በቀል ድርጅትና በአገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች ባለቤትነት ለሚካሄዱ የማሰልጠኛ ተቋማት ፈቃድ (የምዝገባ እና የእውቅና ፈቃድ) የመስጠት ሥልጣን ተቋሙ የሚቋቋምበት ክልል ይሆናል፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. አጠቃላይ

### 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት የፕሮግራም ምዝገባና የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል:: 521/2013

### 1.2. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌ/ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ ፀድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሁሉም የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል::

- በአሁኑ ሰዓት የዕውቅና ፈቃድ ያላቸው ተቋማት ፈቃዱ እንደምዝገባ ፈቃድ የሚያገለግል ሲሆን ይህ መመሪያ ስራ ላይ በዋለ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ግን የዕውቅና ፈቃድ ጥያቄ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል::

### 1.3. ትርጓሜ

- የፕሮግራም ምዝገባ ማለት ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ተቋም በተቋሙ የሚሰጣቸውን ፕሮግራሞች በይፋ ለመጀመር የሚያስችል ሂደት ነው:: የዕውቅና ፈቃድ ማስረጃ ማግኘት እስከሚጠበቅበት ጊዜ ድረስ የስለጠና ፕሮግራሙን እንዲጀምር የሚያስችለው ነው::
- ዕውቅና ማለት ትምህርት ወይም ስልጠና ለሚሰጥ ተቋም ዕውቅና ለመስጠት የሚደረግ የጥራት ማረጋገጫ ሂደት ሲሆን ይህም የሚሆነው ሃላፊነት የተሰጠው የህግ ወይም የሙያ ባለስልጣን ተቋሙ አስቀድሞ የተቀመጡ መለኪያዎችን አሟልቶ መገኘቱን ሲያረጋግጥ ነው::
- የገበያ ፍላጎት ማለት ኢንዱስትሪዉ በሚፈልገው የሙያ ዘርፍ ደረጃ መጠንና ብቃት ያለዉ እስከ መካከለኛ ደረጃ ድረስ ተፈላጊ የሰለጠነ የሰው ሃይል ነው::
- ፕሮግራም ማለት አንድ የቴክኒክና ሙያ ተቋም ስልጠና የሚሰጥበት የሙያ ማዕከል ነው::

- የዕውቅና እድሳት ማለት ትምህርት ወይም ስልጠና የሚሰጥ ተቋም የተሰጠውን ዕውቅና በመጠቀም መመሪያው በሚያስቀምጠው የጥራት ደረጃ መሰረት ስልጠና ሲሰጥ ቆይቶ የተሰጠው የጊዜ ገደብ በመጠናቀቁ ምክንያት የተቋሙን ወይም የፕሮግራሙን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን ሃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን ለተቋሙ ወይም ለፕሮግራሙ አስቀድሞ የተቀመጡ መለኪያዎችን አሟልቶ መገኘቱን ሲያረጋግጥ በድጋሚ ዕውቅና የሚያድስበት ሂደት ነው፡፡
- ተቋም ማለት አንድ የመንግስት ወይም የግል ንብረት የሆነ ትምህርት እና ስልጠና የሚሰጥ የቴ/ሙ/ት/ስ ማዕከል ነው፡፡
- መንግስታዊ ተቋም ማለት አስፈፃሚው አካል ወይም ፈቃድ ሰጪው አካል ነው፡፡
- የሙያ ብቃት ማለት አንድ ሰልጣኝ ስልጠናውን ሲያጠናቅቅ የሚኖረው ዕውቀት ክህሎትና አመለካከት ነው፡፡
- ደረጃ ማለት አንድ ባለሙያ በስራ ቦታ መስራት የሚጠበቅበትን የስራ ውስብስብነት ወይም ክብደት መጠን የተቀመጡ ስራዎችን መሰረት አድርጎ በተቀመጡ ንዑስ የብቃት አሃዶች/unit of competence/የሚመደብ ከ1 እስከ 5 የተለየ ደረጃ ነው፡፡
- ምዘና ማለት የአንድ ባለሙያ ብቃት በብቃት ምዘና ማዕከላት በሚሰጥ የፅሑፍና የተግባር ፈተና የሚረጋገጥበት ሂደት ነው፡፡
- የማጣቀሻ መጽሐፍ ማለት ስልጠና ለሚሰጥባቸው ሙያዎች የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል የጽሁፍ መረጃ ነው፡፡
- ውጤት ተኮር ስልጠና ማለት በገበያ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ በማሰልጠን ባለሙያዎችን ወደ ስራ የማሰማራት አሰራር/አካሄድ ነው፡፡
- ግብአት/input(s)/ ማለት በተቋማት ለአንድ ፕሮግራም የሚያስፈልጉ የማሰልጠኛ ቁሳቁሶችን የሚይዝ ነው፡፡
- የስልጠና አሰጣጥ ሂደት/process (es)/ የቴ/ሙ ተቋማት የሚሰጡት ስልጠና ሰልጣኞችን ለስራ የሚያዘጋጅ እንዲሆን በስራ ገበያው ፍላጎት ላይ ተመስርቶ በትብብር ስልጠና የተደገፈ ሲሆን ማለት ነው፡፡
- ውጤት/Out put/ ማለት በሙያ ምዘና ብቁ መሆናቸው የተረጋገጠ የሰልጣኞች ውጤት ነው፡፡
- ዝቅተኛ መለኪያዎች በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶች እና ፈቃድ ሰጪው አካል የሚያዘጋጀውን "ቼክ ሊስት" ዝርዝር መስፈርቶች ማለት ነው፡፡

- የቦርዱ አካላት ማለት ከተለያዩ የዘርፍ መስሪያቤቶች፣ ኢንዱስትሪዎች የተውጣጡ አመራሮች በተቋሙ ለሚከናወኑ ስራዎች እንደ ውሳኔ ሰጪ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. የምዝገባና የእውቅና ፈቃድ መሰረታዊ ነጥቦችና ጽንሰ ሀሳብ

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አማካኝነት የሚሰጡት ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የሰው ሀይል ገበያውን ፍላጎት፣ ቴክኖሎጂውን፣ አጠቃላይ የአገሪቷን የዕድገት አቅጣጫና ሌሎች ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ እንደየሁኔታው የሚለዋወጡ ሲሆን ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እውቅና የመስጠት ተግባር በአንድ ወቅት የሚከናወን ሳይሆን ተከታታይነት ያለው ስራን የሚጠይቅ ነው፡፡ በአጠቃላይ የእውቅና አሰጣጥ ሂደት የሚከተሉት ሦስት ደረጃዎች አሉት፡፡

1. የምዝገባ ስርዓት ፊ
2. እውቅና ፈቃድና
3. የእውቅና እድሳት ⇒ ዳኅዷሰት

## 2.1. ምዝገባን አስመልክቶ የቀረቡ መሰረታዊ ነጥቦችና ጽንሰ ሀሳብ

ምዝገባ ማለት ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ተቋም በተቋሙ የሚሰጣቸውን ፕሮግራሞች በይፋ ለመጀመር የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑና ሰልጣኞችን ከአደጋ መከላከል ይቻል ዘንድ ተቋሙ ለምዝገባ ሲያመለክት የምዝገባ ሂደቶችን አሟልቶ ስልጣንና ሀላፊነት ለተሰጣቸው ለሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋሞች የሚያሳውቅበት ሂደት ነው፡፡

ተቋሙ ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚጀምረው በዚህ ረገድ ስልጣን የተሰጠው መንግስታዊ አካል በሚያደርገው ግምገማ ተቋሙ ለስልጠናው አስፈላጊ የሆኑ የግብአት መስፈርቶችን ማሟላቱን ሲያረጋግጥና የምዝገባ ፈቃድ ሲሰጠው ብቻ ነው፡፡

ፈቃድ ሰጭው አካል በሚሰጣቸው የፕሮግራም ማስጀመሪያ የምዝገባ ፈቃድም ተቋሙ በፕሮግራሙ ተቀብሎ እንዲያሰለጥን የተፈቀደለትን የሰልጣኞች ብዛት መወሰን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ይህ የምዝገባ ፈቃድ ተቋሙ የዕውቅና ፈቃድ ማስረጃ ማግኘት እስከ ሚጠበቅበት ጊዜ ድረስ የስልጠና ፕሮግራሙን እንዲጀምር የሚያስችለው ነው፡፡

የስልጠና ፕሮግራም ምዝገባ በሚካሄድበት ወቅትም የሚከተሉት የግብአት መለኪያዎች ግንዛቤ ሊወሰድባቸው ይገባል:: እነዚህም፡-

- የአካባቢ የገበያ ፍላጎት መረጃ
- የሰው ሀብት
- የስልጠና አቅርቦቶች ናቸው

### 2.1.1 የገበያ ፍላጎት መረጃ

ስልጠናው ሰልጣኞችን ውጤት አልባና ለስራ የማይጋብዝ እንዳያደርግ ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ለመስጠት ያቀደውን የስልጠና ፕሮግራም በአካባቢውና በአገር ደረጃ ባለው ገበያ ተፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል::

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋሙ የስልጠና ፕሮግራሞቹን በሰው ሀይል ገበያ መረጃ ላይ ተመስርቶ መስጠት ይኖርበታል:: ይህንን የመረጃ ጥናት ያከናወነ ስለመሆኑም በምዝገባው ሂደት ያቀርባል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የእውቅና ፈቃድ ሰጪው አካል ተቋሙ ያካሄደው የሰው ሀይል ገበያ ጥናት ከሰው ሀይል ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑንና አለመሆኑን ያረጋግጣል::

### 2.1.2 የሰው ሀብት

የእያንዳንዱ አሰልጣኝ የሙያ ችሎታ(ብቃት) እና ልምድ አሰልጣኙ የተመደበበትን ደረጃ ማሰልጠን የሚያስችለው መሆኑ በምዘና መረጋገጥ ይኖርበታል:: ከዚህ አኳያም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የአመራርና አሰልጣኞች ብቃት ማዕቀፍ በሁሉም የስልጠና ደረጃዎች የሚመደቡ አሰልጣኞችና አመራሮች ሊኖራቸው የሚገባውን አስፈላጊ ችሎታና ልምድ ስለሚዘረዝር ይህንኑ ሰነድ ስራ ላይ ማዋል የግድ ይላል::

ጥራት ያለው ስልጠና ለመስጠት እንደመስፈርት ሊወሰድ የሚገባው ሌላው ጉዳይ የአሰልጣኝና ሰልጣኞች ጥምረት ነው:: በመሆኑም የአሰልጣኝ ሰልጣኞች ጥምረት ከሙያው አይነት አንፃር ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል:: በዚሁም መሰረት የቴ/ሙ/ት/ስ በተግባር ላይ ያተኮረና የስራ ገበያው በአብዛኛው የሚፈልገው በቴክኖሎጂ የሙያ መስኮች እንደ መሆኑ መጠን አማካይ የአሰልጣኝ ሰልጣኝ ጥመርታ 1 ለ 30 እንደሚሆን ይጠበቃል ቢሆንም የሙያ መስኮችን ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈቃድ ሰጪው አካል

ለየሙያው የአሰልጣኝ ሰልጣኝ ጥመርታ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥመርታ ከ 1 ለ 50 መብለጥ አይኖርበትም፡፡

### 2.1.3 የስልጠና አቅርቦቶች

የስልጠና አቅርቦት አስፈላጊ የሆኑ ሁሉም አይነት መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች፣ በእያንዳንዱ የሙያ ደረጃ መለኪያ የተጠቀሱት እቃዎችን፣ መፃህፍትን፣ ስርአተ ትምህርትን፣ የማሰልጠኛ፣ የማስተማሪያና የመማሪያ ማቴሪያሎችን ወዘተ....ያካትታሉ፡፡

## 2.2. የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መሰረታዊ ነጥቦችና ጽንሰ ሀሳብ

እውቅና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ በስራ ገበያው ተፈላጊ የሆነ ትምህርትና ስልጠና ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ይረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እውቅና ባንድ በኩል የተቀመጠውን መለኪያ ጥራት ያለውና ስኬት ተኮር ስልጠና የመስጠት ግብን አሟልተው የተገኙትን ተቋማት ለማበረታታት በሌላ በኩል ደግሞ አፈፃፀማቸው ከተቀመጠው ደረጃ በታች የሆኑትንና ምንም አይነት መሻሻል የማያሳዩትን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ጠቀሜታው እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

ለቴ/ሙ/ት/ስ ፕሮግራሞች የሚሰጥ ፈቃድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ የስልጠና ፕሮግራሞቹንና የአሰልጣኝ ተቋማትን ጥራት ለማሳደግና ለማስጠበቅ እንደመሆኑ መጠን የስልጠናውን ጥራት ለማረጋገጥ እንዲቻል ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ግብአቶችን (Inputs) የስልጠና አሰጣጥ ሂደቶችን /Processes/ በሙያ ምዘና ብቁ መሆናቸው በተረጋገጠ የሰልጣኞች ምጣኔ ውጤት/Output/ እና ባለሙያዎቹን ከስራ ጋር ከማስተሳሰር አንፃር ያለ ስኬትን/Outcome/ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ሌላው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ በአንድ ተቋም ውስጥ የተለያየ ግብአት፣ ሂደት እና ውጤትን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች የሚሰጥ እውቅና ለፕሮግራሞች እንጂ ለተቋማት መሰጠት የሌለበት መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ መመሪያ ከተቋማት እውቅና አሰጣጥ ይልቅ በፕሮግራሞች እውቅና አሰጣጥ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

በመሆኑም እውቅና አንድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ፤የስልጠና አሰጣጥ ሂደቶችንና በሙያ ምዘና ብቁ መሆናቸው በተረጋገጠ የሰልጣኞች ምጣኔ ውጤት በየጊዜው [illegible] ወደ ተሻለ ውጤት የሚያደርስ ጥራት ያለው የአስተዳደር ስርአት ስራ ላይ [illegible] ጥራት ያለው የአሰራር ስርአት መዘርጋቱን የሚረጋገጥበት ሂደት ነው፡፡ በዚህ

የማረጋገጥ ሂደትም የአካባቢው የሰው ሀይል ገበያ መረጃ፣ የክትትል ሪፖርቶች፣ ጥራት ያለው የአመራር ስርአት ሪፖርትን አስመልክቶ የተሰጡ ግብረ መልሶች፣ አመላካች ጥናት ወዘተ ሊታሰቡ የሚገባቸው ተግባራት ናቸው:: ይህ ዕውቅና ለመስጠት የሚከናወነው ተግባር የመጀመሪያው ሰልጣኝ ቡድን በተመረቀ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እና የቀጣዩ ሰልጣኝ ቡድን ቅበላ ከመፈፀሙ በፊት ነው:: የመጀመሪያው ሰልጣኝ ቡድን ውጤታማነት የሚለካው ለሙያ ምዘና ከተቀመጡት ውስጥ ቢያንስ 50% ብቃታቸው ሲረጋገጥ ነው::

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የስልጠና ተቋሙ አስፈላጊ የሆኑ የግብአት መለኪያዎችን፣ የስልጠና አሰጣጥ ሂደቶችን፣ በሙያ ምዘና ብቁ መሆናቸው በተረጋገጠ የሰልጣኞች ምጣኔ ውጤት እና ባለሙያዎቹን ከስራ ጋር ከማስተሳሰር አንፃር ያለ ስኬትን/Outcome/ መሠረት ያሟላ መሆኑን በቀላሉ ማረጋገጥ ይችል ዘንድ የስልጠና መሳሪያዎችን ዝርዝር (Check list) ማዘጋጀት ይኖርበታል:: ከዚህ አኳያም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለመስማራት የተቋቋሙ ተቋማት ስልጠናቸውን ለመጀመር የሚያስችላቸው ወይም የማያስችላቸው ዋናው ጉዳይ እውቅና ለማግኘት በቅድሚያ የከፈቷቸው የስልጠና ኘሮግራሞች ከተቀመጡት ዝቅተኛ መለኪያዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው ሲረጋገጥ ነው::

ሠልጣኞች ተቀባይነት ያለው ስልጠና ማግኘት መቻላቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት ስልጠና ለመስጠት በሚፈልጓቸው ኘሮግራሞች ላይ እውቅና የማግኘት ግዴታ አለባቸው:: የስልጠናው ጥራትም የሚለካው በሙያ ምዘናና ለኘሮግራሞች በተሰጠ እውቅና ነው:: የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋም የጥራት አመራር ስርአት /Quality Management System/ ተግባራዊ በማድረግ የመጀመሪያ ዙር ሠልጣኞች ሥልጠናቸውን ባጠናቀቁ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እና ሁለተኛ ዙር ቅበላ ከመደረጉ በፊት የእውቅና ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

ተቋማት የትኛውንም አይነት የጥራት አመራር ስርአት መተግበር በሚችሉበት ደረጃ ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል:: የጥራት አመራር ስርአቱ በደንበኛ ፍላጎት፣ የአሠራር ቅደም ተከተሎችን በመመዝገብ፣ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት፣ የግብረ መልስ ማግኛ ዘዴ ላይ በዋናነት እስካተኮረ ተቋሙን ውጤታማ ማድረግ እስካስቻለ ድረስ ይህኛውን አይነት ተብሎ የሚቀመጥ የጥራት አመራር ስርአት የለም:: በሌላ በኩል ለምዝገባ በተሰጠ ፈቃድ ከአንድ ዙር (ከመጀመሪያ ቅበላ) በላይ የእውቅና ፈቃድ ሳይገኝ ሌላ ቅበላ ማድረግ አይቻልም::

# ክፍል ሶስት

## 3. የምዝገባ ፈቃድ

### 3.1. ለምዝገባ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ ሊይዛቸው የሚገቡ መስፈርቶች

ማንኛውም ለምዝገባ ፈቃድ የሚጠይቅ ተቋም በዝቅተኛ ደረጃ ማሟላት ያለበትና ጥያቄውን ለማየት የሚያገለግሉ መነሻ ነጥቦች፡-

#### 3.1.1. ከትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ የተቋሙ ራዕይ ፣ተልዕኮ፣ ዓላማና አሠራርን በተመለከተ

ሀ) ሥልጠናው ሴኩላር መሆን አለበት፣

ለ) ማንኛውም ተቋም ሠልጣኞች የሚቀበልበት ሥርዓት ሃይማኖት፣ ብሔርንና ፆታን መሠረት ያላደረገ መሆን ይገባዋል፣

ሐ) ማንኛውም ተቋም ሠልጣኞችን የሚቀበለው ትምህርት ሚኒስቴር በየዓመቱ ወደ ቴ/ሙ/ት/ስ ለሚገቡ ሠልጣኞች የሚያስቀምጠውን ዝቅተኛ የመቀበያ መስፈርት መሰረት በማድረግ በፈቃድ ሰጪው አካል የተላለፉ ዝርዝር የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን የተከተለ ይሆናል፣

መ) ተቋሙ የምዝገባ ፈቃድ የሚጠይቅባቸው የትምህርት መስኮች የአገሪቷን የሰው ኃይል ገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣

ሠ) ተቋሙ የሙያ ደረጃዎች እና ስርአተ ትምህርትን፣ የአሰልጣኞች ብቃትን፣ የማሰልጠኛ እቃዎችን፣ የስልጠና መሳሪያዎችን፣ ቁሳቁሶችንና የመረጃ መሳሪያዎችን አስመልክቶ የተቀመጡትን ዝቅተኛ መለኪያዎች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፣

ረ) ለስልጠና ሂደቱ ይረዳ ዘንድ ተቋሙ በምቹ ቦታ እና የተሟላ ማስተማሪያ ክፍሎች ያሉት ስለመሆኑና ስለመደራጀቱ የሚያሳይ መሆን አለበት፣

#### 3.1.2. የአስተዳደራዊ ሰነዶች፣

ሀ) አካባቢያዊ የስራ ገበያ ፍላጎት ሪፖርት፣

ለ) ስልጠና ሊሠጥባቸው በታሰበ ሁሉም ፕሮግራሞች ያሉ የኢትዮጵያ የሙያ ደረጃዎች (EOS) (አሠልጣኞች መጠቀም በሚችሉበት ሁኔታ መሆኑ)፣

ሐ) የ[illegible]ንቨስትመንት ፈቃድ (የመንግስት ተቋማትን አይመለከትም)፣

ሠ) ተቋሙ ሥልጠናውን የሚሰጥበት ህንፃ/ካምፓስ በግል ንብረትነት የተያዘ ወይም በፍ/ሕግ አንቀጽ 1731 ወይም በማናቸውም በሕግ ፊት ሊጸና በሚችል ውል ለ5 ዓመታት እንዲያገለግል በኪራይ የተገኘ መሆን አለበት፣

ሰ) የቦርዱ አካላት አወቃቀር (በግልና በመንግስት ተቋማት መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል)፣

ረ) የቴ/ሙ/ት/ስ ፕሮግራሙ በቦርዱ ያለው ተቀባይነት፣ [illegible]

ሠ) ስትራቴጂካዊ እቅድ (ተቋማዊ የልማት እቅድ)፣ [illegible]

ሸ) በአካባቢ ካሉ ካምፓኒዎች ጋር የተደረገ የመግባቢያ ስምምነት (ለትብብር ስልጠና) የትብብር ስልጠናን በተመለከተ ከተቋሙ ጋር በትብብር የሚሰራው ካምፓኒ አሰልጣኞችን ከራሱ ተቋም ማቅረብ ይኖርበታል:: ይህን በተመለከተም የእውቅና ፈቃድ የሚሰጠው አካል በተቋሙና በካምፓኒው መካከል የተደረሰውን የመግባቢያ ስምምነትና አፈፃፀሙን በጥንቃቄ መመርመር ይጠበቅበታል፣ [illegible]

[illegible]

### 3.1.3. የስርአተ ትምህርት መስፈርቶች፣

አንድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ለሚያካሂደው ስልጠና ፕሮግራም በአግባቡ የተቀረፀ ስርዓተ ትምህርት ሊኖረው ይገባል::

በዚህም መሰረት:-

ሀ. የኢትዮጵያ የሙያ ደረጃን መሠረት ያደረገ ስርአተ ትምህርት፣

ለ. ፕሮግራሙ ከገበያው ፍላጎት ጋር የተገናዘበ ሰልጣኙን ለስራ የሚያዘጋጅ ብቁ ዜጋ የሚያፈራና አግባብነት ያለው መሆን ይኖርበታል ::

ሐ. እያንዳንዱ ሞጁል የተሟላ የሞጁል ዓላማ፣ የሞጁል ዲስክሪብሽን፣ የማሰልጠኛ ዘዴዎች፣ የምዘና ዘዴዎች፣ የማሰልጠኛ እና ማጣቀሻ መፅሐፍ በግልጽና በዝርዝር የተዘጋጀለት መሆን አለበት

መ. በሀገር ውስጥ ከዚህ ቀደም ተሰጥቶ የማይታወቅ ፕሮግራም ከሆነ የገበያ ፍላጎት ያለው ለመሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል የሙያ ደረጃም ሊዘጋጅለት ይገባል

ሠ. አግባብነት ያላቸው የማሠልጠኛ ማቴሪያሎች (መፃህፍት፣ የኢንተርኔት አቅርቦት፣ ቪዲዮ ቴፖች፣ ወዘተ...)

ረ. የኢትዮጵያ የሙያ ደረጃ ባስቀመጠው መሠረት አግባብነት ያላቸው የስልጠና ቁሳቁሶች፣ ማቴሪያል ግብአቶች፣

### 3.1.4. የስልጠናና የድጋፍ ሠጪ ሠራተኞች

የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሊኖራቸው ስለሚገባ ተቋማዊ መዋቅር የተደረሰውን ስምምነት መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ የሥራ ደረጃ የተቀመጡትን ተግባራት በአግባቡ ማከናወን የሚያስችል የሙ.ያ ብቃትና ልምድ ያላቸው በቂ የተቋሙ ሰራተኞች ሊሟሉ ይገባል፡፡

ሀ) የአመራሮች ዝርዝርና ያላቸው የትምህርት ደረጃ፣

ለ) ለፕሮግራሙ የተመደቡ ብቃታቸው የተረጋገጠ የቴ/ሙ/ት/ስ አሠልጣኞች ዝርዝርና ያላቸው የትምህርት ደረጃ፣

ሐ) የድጋፍ ሠጪ ሠራተኞች ዝርዝርና ያላቸው የትምህርት ደረጃ፣

መ) የስልጠናና የድጋፍ ሠጪ ሠራተኞች የውል ስምምነት፣

### 3.1.5. የማሠልጠኛ ተቋማት አቅርቦቶች

የማሠልጠኛ ተቋማት ከሚሰጡት የሙ.ያ መስክ አንፃር ለስልጠና ተስማሚ የሆኑ ህንፃዎች ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን ሕንፃዎቹም እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ የማሰልጠኛ ተቋም የሚከተሉትን አቅርቦቶች ማካተት ይጠበቅበታል፡፡

1. ፀጥታ የሰፈነበትና ለስልጠና አገልግሎት ብቻ የሚውል ምቹ ግቢ ወይም ህንፃ
2. የመማሪያ ክፍሎች፣ ወርክሾፖች፣ ላብራቶሪዎች የሰርቶ ማሳያ ክፍሎችና ኮምፒውተር ማዕከል/ክፍል፣
3. አግባብነትና በቂ ቅጂ ባላቸው መፃህፍት የተደራጀ ቤተ መጻሕፍት፣
4. በሚገባ የተደራጁ የኮምፒውተር ክፍሎች (ስልጠናው የሚሰጥ ከሆነ)፣
5. ቢሮዎች/ለስልጠናና ለአስተዳደር ሰራተኞች/፣
6. ሁለገብ አዳራሽ፣
7. ዕቃ ግምጃ ቤቶች፣
8. የመፀዳጃ ክፍሎች፣ (የወንዶች እና የሴቶች)፣
9. በየወርክሾፑ የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ፣
10. በየወርክሾፑ የእሳት ማጥፊያ፣
11. የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች (ተገቢ ሆኖ ሲገኝ)፣

### 3.1.6. የማሰልጠኛ ተቋማት ሕንፃዎች

ስልጠና የሚሰጥባቸው ሕንፃዎች ሲገነቡ ወይም ሲመረጡ በቂ ብርሃን የሚያገኙ መሆኑ፣ የሙቀት/ቅዝቃዜ/ሁኔታ፣ እንዲሁም የወለሉ ክብደት የመሸከም ችሎታ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡ አደረጃጀትና የቦታው አመራረጥ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን አለበት፡፡

1. የመኪና መንገድ መኖር፣
2. የውሃ፣ የመብራትና የስልክ አገልግሎት የተሟላ መሆን፣
3. የመሬቱ አቀማመጥ ለጎርፍ፣ ለከባድ ንፋስ፣ ለፍሳሽና ለመሳሰሉት የተጋለጠ አለመሆን፣
4. ከአጠቃላይ ትምህርትም ሆነ ከስልጠናው ጋር ግንኙነት ከሌላቸው ሌሎች አቅርቦቶች የተለየ የማሠልጠኛ አቅርቦት፣
5. የማሠልጠኛ ተቋሙ ግቢም ሆነ የተቋሙ ሃብቶች ከአጠቃላይ ትምህርትም ሆነ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተለይተው ሙሉ ለሙሉ ለቴ/ሙ/ት/ስ ፕሮግራም ብቻ ማዋል፣
6. አንድ የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋም ከ300 ሜትር በላይ የሚራራቁ ሁለት የማሠልጠኛ ቦታዎች ካሉት እንደ ሁለት ግቢ የሚቆጠር ሲሆን እያንዳንዱ ግቢም ራሱን ችሎ እንደ ቤተመጻህፍት፣ ወርክሾፖችና በመሳሰሉት አቅርቦቶች መደራጀት ይኖርበታል፣
7. ከላይ የተጠቀሱትን ግምት ውስጥ በማስገባት አንድ የቴክኒክና ሙያ ተቋም ሕንፃ ሲገነባ የቦታ ስፋት መለኪያ (Space Standard) ለአንድ ሰልጣኝ የሚያስፈልገው የቦታ መጠን ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ በዚሁ መሠረት ዋና ዋናዎቹ በሠንጠረዥ 1 ውስጥ ተመልክተዋል፣

ሠንጠረዥ 1 የስልጠና ቦታዎች በካሬ ሜትር

| ተ.ቁ | የሥራ ክፍሎች | የቦታ ስፋት ካሬ ሜትር በሰልጣኝ /ጥቅል/ x 30 | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍል | 1.2 m2 | |
| 2 | የኮምፒዩተር ክፍል | 2.2 | |
| 3 | ሁለገብ አዳራሽ | * | |
| 4 | የቴክኒካል ድሮዊንግ ክፍል | (426) | |
| 5 | ቤተ መጻሕፍት | 4 | |
| 6 | ካፍቴሪያ | ***(103) | |
| 7 | ዶርሚተሪ ከእነሎንጁ | 0.6 | |
| 8 | ሁለገብ ቤተሙከራ | 5 | |
| 9 | ወርክሾፖች/ሰርቶ ማሣያ/ | 3 | |
| | ኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂ | | |
| | • ኤሌክትሪክሲቲ | 4.5 | |
| | • ኤሌክትሮኒክስ | 4.0 | |
| | • ማሽን ቴክኖሎጂ | 5.0 | |
| | • ጀኔራል ሜካኒክስ | 6 | |
| | • አውቶ ሜካኒክስ | 6 | |
| | • የጨርቃ ጨርቅ ቴክኖሎጂ | 6 | |
| | ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ | | |
| | • ሀንጻ ግንባታ | 6 | |
| | • መንገድ ግንባታ | 4 | |
| | • እንጨት ሥራ | 6 | |
| | • ንድፍ ሥራ | 4 | |
| | • ቅየሳ | 3 | |
| | የንግድና አገልግሎት ሙያዎች | | |
| | • ሂሳብ አያያዝ | 1.2 | |
| | • የጽሕፈት ሥራ | 1.7 | |
| | • እቃ ግዢ | | |

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Technical & Vocational Education & Training Agency

| ተ.ቁ | የሥራ ክፍሎች | የቦታ ስፋት ካሬ ሜትር በሰልጣኝ /ጥቅል/ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| | ♦ የመረጃ ቴክኖሎጂ | 1.7 | |
| | ♦ ሕግ | 1.5 | |
| | ○ ስፖርትና አካል ብቃት** | | |
| | ♦ እግር ኳስ | | |
| | ♦ መረብ ኳስ | | |
| | ♦ ቅርጫት ኳስ | | |
| | ♦ እጅ ኳስ | | |
| | ♦ የስፖርት ስልጠና አዳራሽ | | |
| | ○ አርት/ስዕል | 6 | |
| | ○ ሙዚቃ | 2.7 | |
| | ○ የዐጉር ሥራ | 3 | |
| | ○ ምግብ ዝግጅት | 3.5 | |
| | ○ የቤት አያያዝ | *(60) | |
| | ○ የሆቴል አገልግሎት | *(60) | |
| | ○ ዳቦ ጋገራ | 3.5 | |
| | ○ ልብስ ስፌት | 3 | |
| | ○ የቋንቋ ቤተሙከራ | 2.2 | |
| | **** | | |

(*) በቅንፍ ውስጥ የተመለከቱት የስፋት ስታንዳርድ በጥቅል የተቀመጡ ናቸው

(**) በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መለኪያ መሠረት የሚደራጅ ይሆናል፡፡

(***) ይህ መለኪያ የአጠቃላይ ሰልጣኞች ቁጥር በሙሉ በአንድ ጊዜ ለማስተናገድ እንዲችል ሆኖ መደራጀት አለበት፡፡

(****) ከላይ በሠንጠረዡ ያልተጠቀሱ ሙያዎችን በተመለከተ የክልል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች በሙያ ደረጃዎች የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ የራሳቸውን ቼክሊስት የሚያዘጋጁ ይሆናል፡፡

### 3.1.7. የመማሪያ ክፍሎች

ከተማሪው ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ ብዛትና ስፋት ያለው የመማሪያ ክፍል ሊኖር ይገባል፡፡ ለአንድ ሠልጣኝ 1.2 ካሬ ሚትር የሆነ ቦታ ታሣቢ ያደረገ በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር ያለውና በበቂና ተፈላጊ ቁሳቁሶች እንደዚሁም ቀጥሎ በተመለከተው መስፈርት መሠረት የተሟላ መሆን አለበት፡፡

**ለመማሪያ ክፍሎች የሚያስፈልጉ ፈርኒቸሮች**

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | መጠን በሴንቲ ሜትር | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ርዝመት | ወርድ | ቁመት | |
| 1 | ዴስክ | 1 | 55 | 100 | 74 | የሰልጣኝ |
| 2 | ጠረጴዛ | 1 | 80 | 120 | 74 | የመምህር |
| 3 | ወንበር | 1 | 40 | 56 | 78 | የመምህር |
| 4 | ወንበር | በሰልጣኞች ቁጥር | 35 | 35 | 77 | የሰልጣኝ |
| 5 | ጥቁር ሰሌዳ | 1 | - | 240 | 120 | በአንድ ክፍል |
| 6 | ማስታወቂያ ሰሌዳ | 1 | - | 500 | 220 | በአንድ ክፍል |

### 3.1.8. ወርክሾፖች/ሰርቶ ማሳያዎች/

1. ሰርቶ ማሳያዎች ተፈላጊውን ችሎታና ክህሎት እንደየስልጠና መስኩ ሊያስጨብጡ በሚችሉ ልዩ ልዩ ማሽኖች፣ማኑዋሎች፣ ኢንስትሩመንቶች፣ የእጅ መሣሪያዎች፣ ቻርቶችና አላቂ ቁሳቁሶች ወዘተ መደራጀት አለባቸው፡፡
2. በተጨማሪም ስፋታቸውም ከሰልጣኞች ቁጥርና መኖር ካለባቸው መሣሪያዎችና ዕቃዎች ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡
3. ወርክሾፖች እንደየጠባያቸው አስፈላጊና ብቃት ያላቸው የስልጠና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡
4. አንድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ(ICT) ተጠቅሞ እንዲሰራና እንዲያሰለጥን ይጠበቅበታል፡፡ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሙያ ለሚሰጠው ሥልጠና የሚደራጀው ክፍል በሰልጣኝ

### 3.1.9. ቤተመጻሕፍት

1) ቤተመጻሕፍት ቢያንስ 25% የሰልጣኞችን አጠቃላይ ብዛት በአንድ ጊዜ ማስተናገድ እንዲቻል ተደርጎ መደራጀት ይኖርበታል፡፡
2) ያሉት መፃህፍትና ጆርናሎችም የቅርብ ጊዜ ማለትም ከ10 ዓመት ወዲህ የታተሙ እና ወቅታዊ ሊሆኑ የሚገባ ሲሆን ዘመናዊ ቴክኖሎጂና የምርምር ውጤቶችን የያዙ መሆናቸውም መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
3) በቤተመፃህፍቱ በቂ የማጣቀሻ መፃህፍትና ማቴሪያሎች ሊኖሩ የሚገባ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከ50 ፐርሰንት በላይ የሚሆነው በተቋሙ ከሚሰጡ ሙያዎች ጋር ቀጥታ ተዛማጅነት ያላቸው መሆን ይኖርበታል፡፡
4) በቂ ብርሃንና ቬንቲሌሽን ያለው
5) በኢንሳይክሎፒዲያ በዲክሺነሪ ጋዜጦች ወዘተ ተሟልቶ መገኘት ይኖርበታል
6) ቤተመፃህፍቱ የቤተ መፃህፍት ባለሙያዎች የሚኖሩት ሲሆን የተቋሙን የስልጠና ጊዜ ተከትሎ ምንጊዜም ለሁሉም ሠልጣኞችና አሠልጣኞች አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
7) ለመረሐ ግብሩ ጠቀሜታ ያላቸው መፅሐፍቶች ዝርዝር እንደ ማጠቃለያ በሚከተለው መልኩ በማመልከቻው ወቅት ለፈቃድ ሰጪው አካል ሊቀርብ ይገባል፡፡

| ተ.ቁ | የመፅሐፉ ርዕስ | የፀሐፊው ስም | የታተመበት ጊዜ | ISBN | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| | | | | ድምር | | |

→ International Standard Book number

### 3.1.10. የስፖርትና የመዝናኛ ማዕከሎች

የስፖርት ሙያዎችን የሚሰጡ ተቋማት የስፖርት ፋሲሊቲዎችን የማሟላት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ስልጠናውን የማይሰጡ ተቋማት ግን አይገደዱም፡፡

## 3.2 መመሪያዎች

እያንዳዱ የዕውቅና ምዝገባ ጥያቄ የሚያቀርብ ተቋም በአግባቡ የተዘጋጁና የተሟሉ፡-

- የስልጠናና ሌሎች ክፍያዎች

- በፌደራልና በክልሉ ከወጡ ዝቅተኛ መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ የመቀበያ መስፈርቶች
- የጊዜ መቆጣጠሪያ /አቴንዳንስ/
- የቴ/ሙ/ት/ስ አሠልጣኞችና ሠልጣኞች የስነ ምግባር ኮድ
- የግብረ መልስ ስርአት (ከቀጣሪ ድርጅቶች፣ ከሠልጣኞችና ከወላጆች)

3.3 ደጋፊ መመሪያዎች

- የሙያ ምክር እና የስራ ቦታ የማመቻቸት አገልግሎት፣
- የትብብር ስልጠና አገልግሎትና የትግበራ እቅድ፣
- የምሩቃን ሁኔታ ጥናት፣
- የጥናትና ምርምር ፕሮግራሞች፣
- የጤና አገልግሎት፣

3.4 የምዝገባ ማመልከቻ መገምገሚያ መስፈርቶች

ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም የሙያ ደረጃዎች እና ስርአተ ትምህርትን፣ የአሰልጣኞች ብቃትን፣ የማሰልጠኛ እቃዎችን፣ የስልጠና መሳሪያዎችን፣ ቁሳቁሶችንና የመረጃ መሳሪያዎችን አስመልክቶ የተቀመጡትን ዝቅተኛ መለኪያዎች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡ እውቅና ሰጪ አካሉም ይህን አሟልተው ለተገኙት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፕሮግራሙን መጀመር የሚያስችላቸውን አስፈላጊውን የምዘገባ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡

ከላይ የተቀመጡት መሰረታዊ የመገምገሚያ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ነጥቦች ሊሟሉ ይገባል፡-

1. የመኪና መንገድ፣ የውኃ፣ መብራት እና ስልክ ያለው ለቴ/ሙ/ት/ስ አመቺ መሆኑ የተረጋገጠ ህንፃ ወይም ግቢ ስለመሆኑ፣
2. የማሰልጠኛው ምድረ ግቢ የከፍተኛ ትምህርት ከሚሰጥበት ቦታ የተለየ መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. ለሙያው ምቹ የሆኑና ተቋሙ ለማሰልጠን ያቀዳቸውን የተማሪዎች ብዛት የሚመጥኑና በቂ መማሪያ ክፍሎች፣ ወርክሾፖች፣ ላቦራቶሪዎች፣ መጋዘኖች እና የኮምፒውተር ማዕከሎች መኖራቸውን፣

4. አግባብነት ባላቸው መፃህፍትና ማጣቀሻዎች የተደራጀ ቤተመጻህፍት ያለው መሆኑን በተለይ በኢንተርኔትና በኤሌክትሮኒክ ላይብራሪ የተደገፈ ቢሆን ይመረጣል፣
5. በአስፈላጊ ቁሳቁሶች የተደራጁ የስልጠናና የአስተዳደር ሠራተኞች ክፍሎች፣
6. ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውል የሚችል አዳራሽ፣
7. ሠልጣኞችን ማዕከል ያደረገ የመዝናኛ አገልግሎቶች፣
8. የክሊኒክ አገልግሎት ለማግኘት ያለው አመቺነት (ከ300 በላይ ሠልጣኞችን የሚያስተናግድ ተቋም ከሆነ በግቢው ውስጥ ክሊኒክ ያለው መሆኑን ወይም በቅርብ ርቀት ክሊኒክ መኖሩን ወይም በቅርብ ካለ ክሊኒክ ጋር የተደረገ የውል ስምምነት ወዘተ... ማሣየት ያለበት ሲሆን ይህም ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የሚታይ ይሆናል፡፡)
9. የወንዶችና የሴቶችን በሚል ተለይቶ የሚገኝ በቂ የመፀዳጃ አገልግሎት
10. በእያንዳንዱ ወርክሾፕ የደህንነትና የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና እርዳታ መስጫ ማጥኖች፣
11. በእያንዳንዱ ህንፃ ላይ የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣
12. በስልጠና ወቅት ለሙያው የሚያስፈልጉ የደህንነት እቃዎች (ገዋን፣ የአይን መከላከያ ጭምብል፣ ጫማዎች፣ ወዘተ...)
13. ከሙያውና ሙያው ከሚጠይቀው ስታንዳርድ አንፃር ተቀባይነት ያለው የመማሪያ ክፍሎችና የተፈጥሮ ብርሃን ያለው የማሠልጠኛ ወርክሾፕ፣
14. ከሙያውና ከስታንዳርድ አንፃር ተቀባይነት ያለው የአየር ዝውውር፣
15. ከስታንዳርዱ አንፃር በማሽኖች መካከል ያለው ስፋት ተቀባይነት
16. በማህተም የተደገፈ የስልጠና አቅርቦቶች ዝርዝር ሰነድ

### 3.5 የምዝገባ ክፍያ

- ለፕሮግራም አይነቱ ፈቃድ ሰጪው አካል በኩል የተቀመጠ የማመልከቻ ክፍያ መጠን፣
- ለፕሮግራም አይነቱ በክልል የእውቅና ፈቃድ ሠጪ አካል በኩል የተቀመጠ የምዝገባ ክፍያ መጠን፣
- ክፍያው ለኤጀንሲው ገቢ ተደርጎ የዕውቅና ምዝገባ ጥያቄ ሲቀርብ ደረሰኙ መቅረብ አለበት፡፡

## 3.6 የምዝገባ ፈቃድ ስለመስጠት

1) ማንኛውም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም በክፍል ሶስት የተቀመጡትን የግብአት መለኪያዎች አሟልቶ ሲገኝ የስልጠና ፕሮግራሙን መጀመር የሚያስችለውን የምዝገባ ፈቃድ ይሰጠዋል።

2) በፈቃድ ሰጪው አካል የሚሰጥ የምዝገባ ሠርተፊኬት የፕሮግራሙን ወይም የሙያውን ስም፣ ደረጃውን እና በፕሮግራሙ ተቀብሎ ማሠልጠን የሚችለው ከፍተኛውን የሠልጣኝ ቁጥር የያዘ መሆን ይኖርበታል።

3) የምዝገባ ፈቃድ የተሰጣቸው ተቋማት በተፈቀደላቸው ፕሮግራም ፣የሙያ ደረጃ፣ስርዓተ ትምህርትና የተማሪዎች ቁጥር መሰረት ስልጠና መስጠት ይችላሉ።

4) የሚሰጠው የምዝገባ ፈቃድ የሚያገለግለው የመጀመሪያው ዙር ሰልጣኝ ለሙያ ምዘና እስከሚቀመጡ ሲሆን ከተመዘኑት ሰልጣኞች ውስጥ 50 በመቶ የሚሆኑት ብቁ መሆናቸው ከተረጋገጠ ለእውቅና ፈቃድ ማመልከቻ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል።

5) የምዝገባ ፈቃድ የተሰጣቸው ተቋማት የተፈቀደላቸውን ፕሮግራም፣ የብቃት ደረጃ አይነት እና የሰልጣኝ ብዛት የሚገልጽ የምዝገባ ማስረጃ ተመዝጋቢዎች ሊያዩት በሚችሉበት ቦታዎች ላይ ማኖር ይጠበቅባቸዋል።

# ክፍል አራት

## 4 የዕውቅና ፈቃድ

### 4.1 የዕውቅና ፈቃድ መገምገሚያ መስፈርቶች

1. የሙያ ምዘናን የማሟለፍ መጠን ቢያንስ 50% ሊሆን ይገባል (ስልጠና ካጠናቀቁት ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ የሚሆኑት የሙያ ምዘናን ማለፍ ይኖርባቸዋል)
2. እየጨመረ የመጣ የሙያ ምዘናን የማለፍ መጠን በመቶኛ፣
3. እየጨመረ የመጣ ወደ ስራ የተሰማሩ ምሩቃን መጠን፣
4. የተሻሻለ የሙያ ደረጃን (ካለ) ተከትሎ የተሻሻለ ስርአተ ትምህርትና የማስተማሪያ የማሠልጠኛና የመማሪያ ማቴሪያሎች፣
5. የተሻሻሉ የስልጠና አቅርቦቶች እና ያለው ውጤታማ አጠቃቀም፣
6. የተቋማዊ የልማት እቅድ አተገባበርና አረዳድ፣
7. እየጨመረ የመጣ ብቃታቸው የተረጋገጠ መምህራን በደረጃና በመቶኛ፣
8. ስልጠና አጠናቀው የወጡ ባለሙያዎች ያሉበትን ሁኔታ የሚያሣይ የጥናት ሪፖርት (Tracer Study)፣
9. ፈቃድ ባለው የሒሣብ ባለሙያ የተደረገ የኦዲት ሪፖርት፣
10. የተከማቸና የተሸጋገረ ቴክኖሎጂ፣
11. በአካባቢው ካለ ኢንዱስትሪ ጋር የተደረገ ከፕሮግራሙ ጋር ተዛማጅነት ያለው የመግባቢያ ስምምነት አተገባበር፣
12. በተቋሙ ድጋፍ አማካኝነት የተደራጁ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ብዛት፣
13. የጥራት አመራር ስርአት /Quality Management System/ ትግበራ የሚያሳይ መረጃ፣
14. በዚህ የማረጋገጥ ሂደትም የአካባቢው የሰው ሀይል ገበያ መረጃ፣ የክትትል ሪፖርቶች፣ ጥራት ያለው የአመራር ስርአት ሪፖርትን አስመልክቶ የተሰጡ ግብረ መልሶች፣ አመላካች ጥናት

## 4.2 ለዕውቅና ፈቃድ መሟላት ያለባቸው ነጥቦች

ሀ). ሂደት /Process/

ለቴ/ሙ/ት/ስ ፕሮግራም የሚያስፈልጉ ግብአቶች በምዝገባ ፈቃድ ደረጃ የተፈተሸ በመሆኑ የእውቅና ፈቃድ በዋናነት የሚያተኩረው በስልጠናው ሂደት /Process/ እና ውጤት ላይ ይሆናል፡፡ ለእውቅና ፈቃድ የሚያመለክት ተቋም ከስልጠና ሂደትና ውጤት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ደጋፊ መረጃዎች የእውቅና ፈቃድ ለሚሰጠው ኤጀንሲ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

- የሠልጣኞች ቅበላ(መስፈርትን ጨምሮ)
- የስርአተ ትምህርት ዝግጅት/ማሻሻያ/
- የስልጠና አሰጣጥ
- የማሠልጠኛ ማቴሪያሎች አግባብነት
- በተቋሙ ደረጃ ያለው የሠልጣኞች ምዘናና የስልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሠራር
- በምዝገባ ጊዜ ውስጥ የነበረው የሀብት አጠቃቀም ተገቢነት
- ተከታታይነት ያለው አካባባቢያዊ የስራ ገበያ ፍላጎት ዳሰሳ
- የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ተግባራት
- ከኢንዱስትሪ ጋር ያለው ትስስር (በትብብር እና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና)
- የታደሰ የንግድ ፈቃድ
- ከላይ በተዘረዘሩት ሁሉም ተግባራት ላይ ያለው የሰነዶች አያያዝ ሁኔታ

ለ). ውጤት/Out put/

- በያመቱ አገር አቀፍ የሙያ ምዘናን ማለፍ የቻሉ ምሩቃን መጠን በቁጥርና በፐርሰንት
- ወደ ስራ የተሰማሩ ምሩቃን መጠን፣
- በተቋሙ ድጋፍ አማካኝነት የተደራጁ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ብዛት፣

በፈቃድ ሰጪ አካል የሚሰጠው የእውቅና ማስረጃ ፈቃድ እውቅና የተሰጠበትን የፕሮግራም ስም፣ ደረጃውን እና ለፕሮግራሙ የተፈቀደውን የሠልጣኝ ብዛት የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 4.3 የዕውቅና ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ

ከእውቅና፣ የማረጋገጫ ሰርተፊኬትና ከሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ የአገሎግሎት ክፍያ በክልል መስተዳድር ወይም በፌደራል ዋና ከተማ መስተዳድር የሚመለከተው ባለስልጣን አማካኝነት መወሰን ይኖርበታል፡፡

## 4.4 የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

እውቅና መስጠት የብቃት ማረጋገጫ ሂደትም ሲሆን በአንድ በኩል የትምህርት ወይም የስልጠና ኘሮግራሙን የሚሰጠው ተቋም በእውቅና ሰጪው አካል የተቀመጡትን የጥራት መለኪያዎች አሟልቶ መገኘቱን ለህዝብ የሚገለጽበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የስልጠናው ኘሮግራም በእውቅና ሰጪው አካል ይሁንታ ማግኘቱ ተቋሙ የጥራት መለኪያዎችን ለማሟላትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኘሮግራሞችን አቅርቦት ጥራት ለማሻሻል በማሰብ እራሱን በሂደት ለመፈተሽና በውጭ አካል ለማስገምገም ዝግጁ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ህብረተሰቡ ሁሉንም የምዝገባና የእውቅና ፈቃድ ያላቸውን ማወቅ እንዲችሉ ፈቃድ ሰጪው አካል በክልል ያሉ ሁሉም ተቋማት ያሉበትን ደረጃ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም አሠራር በክልሉ የቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ ወይም ተመሣሣይ ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣን የመረጃ መረብ /web page/ ላይ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ቢፈጠር ተመራጭ ይሆናል፡፡

የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት ያሉበትን ደረጃ የሚያሣይ አገር አቀፍ የመረጃ ቋት በፌደራል ደረጃ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ የሚውል ሲሆን መረጃዎቹም በየመቱ፡ እየታደሱ የሚወጡ ይሆናሉ፡፡ ይህም በፌደራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ የመረጃ መረብ አማካኝነት ለህዝብ ይፋ የሚደረግ ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት የቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች/ ኮሚሽኖች፡-

4.4.1 በክፍል 4.1 እና 4.2 የተቀመጡ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ገምግሞ በማረጋገጥ የዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል

4.4.3 የሚሰጠው የዕውቅና ፈቃድ የሚያገለግለው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ዓመት ብቻ ይሆናል። በዚህ ፈቃድ ዕውቅናውን በወሰደበት ወቅት ሰልጣኞችን መመዝገብ ያልቻለ ተቋም ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት ጥያቄውን በድጋሚ ማቅረብ ይኖርበታል

4.4.4 የዕውቅና ፈቃድ የተከለከለ ተቋም የፈቃድ ክልከላው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ ከ ሶስት ወር በኋላ አስፈላጊ የሆኑትንና የተጓደሉትን መመዘኛዎች በማሟላት እንደገና ማመልከት ይችላል ሆኖም የዕውቅና ፈቃድ ዳግመኛ የተከለከለ አመልካች ዳግም ከተከለከለ ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ሊያመለክት ይችላል

4.4.5 በድጋሚ የዕውቅና ፈቃድ የተከለከለ ተቋም የተቀበላቸውን ሰልጣኞች አግባብ ባላቸው ሌሎች ተቋማት ተዛውረው ስልጠናቸውን እንዲያጠናቅቁ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል

## 4.5 የዕውቅና ፈቃድ ስለመሰረዝ

የቴ/ሙ/ት/ስ ፕሮግራም ከዚህ በታች በተጠቀሱት በየትኛውም ምክንያት ሊሰረዝ ይችላል።

- በምዝገባም ሆነ በእውቅና አሰጣጥና በእውቅና እድሳት ሂደት ወቅት የሚሰጡ ማንኛውም አይነት የተሣሣቱ መረጃዎች፣
- በምዝገባም ሆነ በእውቅና አሰጣጥና በእውቅና እድሣት ደረጃዎች የታየ የትኛውም አይነት የመስፈርቶች ጥሰት፣
- በሚመለከተው ክልል የሚቀመጠውን ደንብና የመግቢያ መስፈርትን ያልተከተለ የሠልጣኞች ቅበላ፣
- ማንኛውም ተመዝግቦ ያለ ፕሮግራም በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ የእውቅና ፈቃድ ካላገኘ፣
- ማንኛውም እውቅና ያለው ፕሮግራም በየ 3 አመቱ ካልታደሰ፣
- የስልጠና ፕሮግራም በሚሰረዝ ጊዜ የሠልጣኞች የወደፊት እድል በጥንቃቄ ሊያዝና ሊስተናገድ ይገባዋል።

# ክፍል አምስት

## 5. የዕውቅና ዕድሳት

ስልጠና ሰጪ ተቋማት የአካባቢውንና ሀገራዊውን የሰው ኃይል ፍላጐት እስካሟሉና የስልጠና ኘሮግራሞቹ ሀገራዊውን የልማት ግብ በማሳካት ሀዲድ ላይ እስካሉ ድረስ በስራው ውስጥ እንዲቆዩ የሚያስችል የእውቅና እድሳት በመስጠት ሂደት ህብረተሰቡን ጥራት አልባ ከሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ውጤት አቅርቦት ለመከላከል የሚያገለግል ነው፡

### የዕውቅና ዕድሳት መገምገሚያ መስፈርት

እውቅናን የማደስ ስራ የሚያተኩረው በቴ/ሙ/ት/ስ ኘሮግራሙ ሂደትና ስኬታማነት ላይ ነው፡፡ ይህም ኘሮግራሞቹ ከሰው ኃይል ገበያው ፍላጐት አንፃር ሊቀጥሉ የሚችሉ መሆናቸውና ቀጣይነት ያለው መሻሻል መኖሩን ለማረጋገጥ የሚረዳ ነው፡፡በመሆኑም በተቻለ መጠን የስልጠና ብክነትን መቀነስ ያስችላል፤ የኘሮግራሙን ቀጣይነትም ያረጋግጣል፡፡ ይህ ደግሞ አጠቃላይ የስልጠናው ሂደት በማህበረሰቡ ስኬታማነት ላይ በጐ ተፅእኖ መፍጠሩንና አለመፍጠሩን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

1. የኘሮግራሞቹ እድሳት (የእውቅና እድሳት) እንደ ኘሮግራም ቆይታው በተቋሙ ላይ በየጊዜው የሚደረግ ምርመራን መሰረት በማድረግ በየ3 አመቱ የሚደረግ ሲሆን ይህንን ሳያመለክት የቀረ ማንኛውም ተቋም ኘሮግራሙ የማይታደስለት ይሆናል፡፡
2. ለተቋማት አስተድሞ ሳይገለጽ ድንገተኛ የሆነ ግምገማ ሊደረግ የሚችል ሲሆን በዚህም የተገኘው ሪፖርት መጨረሻ ላይ ለእውቅና እድሳት በግብአትነት የሚያገለግል ይሆናል፡፡
3. ፈቃድ ሠጪው አካል በግምገማ ያገኛቸውን የትኛውንም አይነት የአሠራር ግድፈቶች በ6 ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያሻሽሉ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡
4. ከስልጠና ኘሮግራሙ ተመራቂዎች ውስጥ በሀገራዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ብቁ ሆነው የተገኙትንና በግልም ሆነ በቅጥር ስራ ያገኙት ሰልጣኞች ብዛት ባለፉት ሦስት ዓመታት እየጨመረ የመጣ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
5. ከ50% [illegible]

አካል ከሚመለከተው አካል የዕውቅና ወይንም የዕውቅና ዕድሳት ካላገኘ ስልጠና ሊሰጥ አይችልም፡፡

## 5.1 የዕውቅና ዕድሳት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚይዛቸው ነጥቦች

ስልጠና ሲሰጥ የቆየ ተቋም የዕውቅና ፈቃድ ጊዜ በመገባደዱ ምክኒያት ስልጠናውን ለመቀጠል የሚፈልግ ማንኛውም አካል አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት መጠየቂያ ማመልከቻ በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ (Check List) መሰረት ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ ማመልከቻ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ያሚላ ሲሆን ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

1. በየዓመቱ ተቋሙ በሚሰጠው በእያንዳዱ ፕሮግራም የተመዘገቡ አጠቃላይ የሰልጣኞች ቁጥር
2. በየዓመቱ አገር አቀፍ የሙያ ምዘናን ማለፍ የቻሉ ምሩቃን መጠን በቁጥርና በፐርሰንት
3. በግልም ሆነ በቅጥር ስራ ያገኙት ሰልጣኞች ብዛት
4. ከኢንዱስትሪ ጋር ያለው ትስስር (በትብብር እና በኩባንያ ውስጥ ስልጠና)
5. የተከማችና የተሸጋገረ ቴክኖሎጂ፡ ብዛት
6. የጥራት አመራር ስርአት /Quality Management System/ ተግባራዊ በማድረግ
7. የዕውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም ቀደም ሲል እንዲታደስ ሲጠይቅ ለኤጀንሲው ከቀረበው ማመልከቻ ጋር ቀርበው የነበሩትን መረጃዎች፣ የስልጠና ግብዓቶች፣ ሂደቶች እና ውጤቶች አሁን ያሉበት ደረጃ የሚገልፅ ሪፖርት
8. የክንዋኔ ሪፖርት
9. ተቋማት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ማቅረብ ያለባቸው የእውቅና ፈቃዱ ከመጠናቀቁ ስድስት ወር በፊት መሆን አለበት

## 5.2 የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ስለመስጠት

የቴ/ሙ/ት/ስ ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች/ ኮሚሽኖች:-

1. በክፍል 5.1 እና 5.2 በተጠቀሰው መሰረት የዕውቅና ዕድሳት ጥያቄዎች

- ስርዓተ ትምህርትን፣ የስልጠና ጥራት፣ ሰልጣኞች በስለጠና ሂደት ያላቸው ተሳትፎ፣ የአሰልጣኞች ብቃት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛች የትምህርት ደረጃ በጥልቀት ገምግሞ በማረጋገጥ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ይሰጣል፡፡

3. የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት የተሰጣቸውን ተቋማትና መርሐግብሮች ዝርዝር አመቺ በሆነ ሚዲያ ለህብረተሰቡ ያሳውቃል
4. የሚሰጠው የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት የሚያገለግለው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡
5. የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት የተከለከለ ተቋም የፈቃድ ክልከላው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ ከሶስት ወር በኋላ አስፈላጊ የሆኑትንና የተጓደሉትን መመዘኛዎች በማሟላት እንደገና ማመልከት ይችላል ሆኖም የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ዳግመኛ የተከለከለ አመልካች ዳግም ከተከለከለ ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ሊያመለክት ይችላል፡፡
6. በድጋሚ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት የተከለከለ ተቋም የተቀበላቸውን ሰልጣኞች አግባብ ባላቸው ሌሎች ተቋማት ተዛውረው ስልጠናቸውን እንዲያጠናቅቁ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

## 5.3 የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ክፍያ

ከእውቅና፣ የማረጋገጫ ሰርተፊኬትና ከሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ የአገልግሎት ክፍያ በክልል መስተዳድር ወይም በፌደራል ዋና ከተማ መስተዳድር የሚመለከተው ባለስልጣን አማካኝነት መወሰን ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ስድስት

### 6. የማታና የርቀት ትምህርትና ስልጠና

### 6.1 የርቀት ትምህርትና ስልጠናን በተመለከተ

የርቀት ትምህርትና ስልጠናን በተመለከተ በአሁኑ ወቅት በቴክኖሎጂው ብቁ የሆኑና ከኢንዱስትሪው በሚቀርበው ፍላጎት መሰረት የተሟላ ስልጠና መስጠት የሚችሉ ተቋማት ባለመኖራቸው ስለርቀት ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች እውቅና አሰጣጥ በዚህ መመሪያ የሚዳሰስ አይሆንም፡፡ ስለሆነም የአገራችንን የስልጠና ጥራት ከማስጠበቅ አንፃር ይህ መመሪያ የትኛውንም በርቀት ለማሰልጠን የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ የማያስተናግድ ይሆናል፡

### 6.2 የማታ ስልጠናን በተመለከተ

ይህ መመሪያ በዋናነት ያተኮረው በተቋሙ በቀኑ ፕሮግራም መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ስልጠናዎችን ለማሠልጠን የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን በማታው ፕሮግራም ለማሰልጠን ሲፈለግ ተቋማት የፈቃድ ሰጪውን ይሁንታ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ፈቃድ ሠጪ አካላትም ጥያቄውን የሙያው ባህሪይ በማታው የስልጠና ፕሮግራም ለመስጠት ያለው አመቺነትና ተገቢነት እንዲሁም በስልጠናው ጥራት ላይ የሚኖረውን ተፅህኖ ከግምት በማስገባትና ከሙያው ጋር ቅርብ ቁርኝት ካላቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ሊያስተናግዱ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ የፈቃድ ሠጪውን አካል ይሁንታ አግኝቶ በማታው ፕሮግራም ለማሠልጠን የሚፈቀደው የሠልጣኝ ብዛት ተቋሙ ለቀኑ ፕሮግራም ከተሰጠው የሠልጣኝ ብዛት መብለጥ አይኖርበትም፡፡